**የካምብሪጅ ከተማ**

# የቤት ተከራዮችን የሚመለከት የመኖሪያ ቤት መብቶችና መረጃዎች

**የኮቪድ-19 ወረርሺኝ በአያሌ ሰዎች ላይ የገንዘብ ጉዳት ያስከተለ ሲሆን City of Cambridge (የካምብሪጅ ከተማ) የቤት ተከራዮችን ለመጠበቅና ከመኖሪያ ቤት ጋር በተገናኘ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ግብአቶችና ፕሮግራሞች አሉት። Cambridge (በካምብሪጅ) ውስጥ ያሉ የቤት ተከራይ ከሆኑ፣ ለእርስዎ የሚያገለግሉ በርከት ያሉ መብቶችና ግብአቶች ይገኛሉ።**

## በቤት ኪራይ ዙሪያ የሚደረግ እገዛ



- የቤት ኪራይዎን ያልከፈሉ ከሆነ፣ ወደ **Cambridge Multi-Service Center (ካምብሪጅ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ማዕከል)**
  በ **617-349-6347**በመደወል ላይ እገዛ ያግኙ።
- የከተማው **Housing Stabilization Program (የመኖርያ ቤትን የማረጋጋት ፕሮግራም)**
  በካምብሪጅ ውስጥ የመኖሪያ ቤት አለመረጋጋት ችግር እያጋጠማቸው ላሉ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።
  - ስለ ብቁ መሆን እና ማመልከት እንዴት እንደሚቻል ለማወቅ፣ **www.cambridgema.gov/HousingFund**ይጎብኙ።
- **ጥያቄ? የ Multi-Service Center (ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ማዕከል)** ወይም **City's Housing Liaison (የከተማው መኖርያ ቤት አስፈፃሚ አካል)**
  ን በ **617-349-6337**ያነጋግሩ።

## ከኪራይ ቤት ማስለቀቅን የሚመለከት መረጃ

የከተማው ተከራዮችን በሃይል ከቤት የማስለቀቅ ሂደት ላይ የከተማው ያወጣው ጊዜአዊ አስቸኳይ ትዕዛዝ በስራ ላይ እንዳለ ይቆያል።

ይህም ማለት:



- ቤት አከራዮች ሃይል አስገድደው ቤት ተከራዮችን ከተከራዩበት ቤት እንዲወጡ ማድረግ አይችሉም። **የቤት አከራይዎ ከተከራዩበት ቤት እንዲለቁ ስለነገርዎት ወይም በወረቀት ማሳሰቢያ ስለሰጡዎት ከተከራዩበት ቤት መልቀቅ አያስፈልግዎትም።**
- ከአከራይዎ የቤት ልቀቁ ማሳሰቢያ ከደረስዎት፣ ሊከተሉት የሚገባ የፍርድ ቤት ሂደት አለ። **ሕጋዊ ምክርና አገልግሎቶቸን ይፈልጉ፣ ቤትዎንም ለቀው አይሂዱ።**
- ህጋዊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲረዳዎት የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ **www.masslegalhelp.org** አሊያም ደግሞ **www.gbls.org/MADE** ይጎብኙ ወይም ወደ City's Housing Liaison (የከተማው መኖርያ ቤት አስፈፃሚ አካል) በ **617-349-6337**ይደውሉ።

**የካምብሪጅ ከተማ**

# የቤት ተከራዮችን የሚመለከት የመኖሪያ ቤት መብቶችና መረጃዎች

## የተከራዮች መብቶችና ግብአቶች

- የከተማው የ 2020 የቤት ተከራዮች መብቶችና ግብአቶች ማሳወቂያ ሕግ ቤት አከራዮች ቤት ማከራየት ማቆማቸውን ሲያሳስቡ፣ የኪራይ ዉል እንደማያድሱ ሲያሳስቡ፣ ወይም ደግሞ የኪራይ ጊዜው ማለቁን ሲያሳስቡ የቤት ተከራዩን መሰረታዊ መብቶችና ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ግብአቶችንም እንዲሁ አብረው ለቤት ተከራዩ መስጠታቸውን የሚያሳይ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ያዛል።
- የተከራዮችን መብቶችና ለተከራዮች ያሉትን ግብአቶች በበለጠ ይወቁ: **www.cambridgema.gov/TenantRights**